# በትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለስልጣን የአደገኛ ዕቃዎች ማጓጓዣ መመሪያ ቁጥር 691/2013

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

ግንቦት 2006ዓ.ም

# የአደገኛ ዕቃዎች ማጓጓዣ መመሪያ ቁጥር 06/2006

## መግቢያ

ለትራንስፖርት ባለስልጣን ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት መካከል አንደኛው በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7/1/ረ መሠረት መንገደኞች፣ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈፃፀሙን መከታተል በመሆኑ የአደገኛ ዕቃዎች ማጓጓዣ መመሪያ ማውጣትና ተግባራዊነቱንም መከታተል፣ የአደገኛ ዕቃዎች ሲጓጓዙ በጥንቃቄ ጉድለት በሰውና በንብረት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል እንዲያስችለው መመሪያ መውጣቱ አስፈላጊነቱ በመታመኑ እንደሚከተለው መመሪያው ወጥቶዋል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ " የአደገኛ ዕቃዎች ማጓጓዣ መመሪያ ቁጥር 691/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጥ ካላስፈለገ በስተቀር በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 2 የተዘረዘረው የቃላት ትርጉም በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ የሚከተሉት ተጨማሪ ቃላትም ከታች የተዘረዘሩት ትርጉም ይኖራቸዋል፣

   1. " አደገኛ እቃ" ማለት በባህሪያቸው አደጋ የሚያመጡ ዕቃዎች ወይም አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው የተመደቡ ተቀጣጣይ የሬዲዮ ሞገድ ማመንጨት የሚችሉ በጤንነት ላይ አደጋ ማስከተል የሚችሉ የንጥረ ነገር ወይም የጋዝ ባህሪ ያላቸው ወይም የሰው ልጅ ጤንነትና አካባቢ ላይ ጥፋት ማስከተል የሚችሉ ዕቃዎች ማለት ነው፡፡

   2. " የታመቀ ጋዝ " ማለት እንደ አየር፣ አርጐን፣ ካርቦን ሞኖኦክሳይድ፣ የከሠል ጋዝ፣ ሀይድሮጂን፣ሚቴን፣ ኦክስጅን፣ ሰልፈርዳይኦክሳይድ፣ እንደ አሞኒያ ያለ በብረት ሲሊንደር ውስጥ ታምቆ የሚጓጓዝ ንጥረ ነገር ነው፣

   3. " አሲድ ወይም ዝገት ነክ ንጥረነገር " ማለት የሀይድሮጂን ውሁድ ያለበት ፈሳሽ ኬሚካል ሆኖ የአሲድነት ልኬቱ ከ7 ፒኤች ያነሰ ማናቸውም ንጥረ ነገር ነው፣

4. " ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር ወይም ጋዝ " ማለት ከ23 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ወይም ከ73 ዲግሪ ፋራናይት በታች በሆነ ሙቀት የተቀጣጣይነት ነበልባል የሚሰጡ ኬሚካሎች ውህድ ወይም ድብልቅ ነው፣

5. " ቦቴ " ማለት አደገኛ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ ተብሎ ከተሽከርካሪው ፍሬም ጋር ተያይዞ የተሠራ ማጓጓዣ ነው፣

6. " ኮንቴይነር " ማለት ከ3 ኪዩቢክ ሜትር በላይ አደገኛ ዕቃዎችን የመጫን አቅም ያለው ተንቀሣቃሽ ኮንቴነር ነው፣

7. " አጓጓዥ" ማለት አደገኛ ዕቃዎች በማጓጓዝ ሥራ ላይ የተሠማራ ተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም አሽከርካሪ ነው፣

8. " ሬዲዮ አክቲቭ ቁስ" ማለት ማንኛውም ከቁጥጥር ነጻ ተብሎ ከሚወጣው መጠን በላይ የሆነ አዩን ፈጣሪ ጨረር አመነጪ ቁስ ነው፣

9. " መርዛማ ቆሻሻ " ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው፣

10. " መርዝ" ማለት ፈሳሽ፣ ጥጥር ወይም ጋዝ የሆነ ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጉድል ወይም በሰው ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርስ ማለት ነው፣

11. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣

12. “ባለስልጣን” ማለት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመ ትራንስፖርት ባለስልጣን ነው፡፡

**3. የመመሪያው ተፈፃሚነት**

1. ይህ መመሪያ አደገኛ ዕቃዎችን ጭኖ በኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚሽከረከር ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

4. <u>መግለጫ ስለመለጠፍ</u>

1. አደገኛ ዕቃዎችን የሚያጓጉዝ ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪ ስለሚኖረው አደገኛ ዕቃ የሚያብራራ ከተሽከርካሪው ፊትና ኋላ ስፋቱ ከ 50.97 ስኬዌር ሣንቲ ሜትር እንዲሁም በኮንቴይነር በሚሆንበት ጊዜ ጐንና ጐኑ ላይ ከ25.16 ስኬዌር ሣንቲ ሜትር ያላነሰ መግለጫ መለጠፍ አለበት፣

2. የዕቃ መግለጫ ሳይቀርብለት እነዚህን አደገኛ ዕቃዎች በመጠኑና በማጓጓዝ ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት አጓጓዡ ኃላፊ ነው፣

3. እቃዎች በኃላፊነት ተወስደው የተጓጓዙት የአደገኝነት ባህሪያቸውን የሚገልጽ መግለጫ ሳይቀርብለት ከሆነ በማናቸውም ሰው በመከላከያነት ሊጠቀሱ አይችሉም፣

4. አደገኛ ዕቃን በማጓጓዝ ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በተገቢዎቹ ደረጃዎች መሠረት መመዝገቡን፣መታሸጉንና ምልክት የተለጠፈበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣
5. ዕቃ አስረካቢው በተገቢ ሁኔታ አደገኛ ዕቃውን አደገኛ በማለት ማመልከት ወይም በሚለጠፍ ነገር ማሣየት አለበት፣

6. ስለዕቃዎቹ ዝርዝር መግለጫ የዕቃውን ባህሪ እና የአስተሻሸግ ዘዴ እንዲሁም አደገኛ ዕቃዎች በሆኑ ጊዜ የታወቀው አጠቃላይ ባህሪያቸው መግለጫ መስጠት አለበት፣

7. ዕቃ አስረካቢው አደገኛነት ያላቸውን ዕቃዎች ለአጓጓዡ ባስረከበ ጊዜ ለአጓጓዡ የዕቃውን የአደገኛነት ባህሪ እና አስፈላጊ በሆነም ጊዜ ሊወሰድ የሚገባውን የጥንቃቄ እርምጃ በትክክል ማሳወቅና ማመልከት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ስለማጓጓዝ</u>

5. <u>አሲድ ወይም ዝገት ነክ ንጥረ ነገር</u>

1. ማናቸውም አሲድ ወይም ዝገት ነክ ንጥረ ነገር አጓጓዥ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፣

ሀ. 14.50 ኪዩቢክ ሜትር / 512.1 ኪዩቢክ ጫማ/ ወይም ከቦቴ ላይ ቦቴ ከሆነ የጭነት ኮንቴይነር ውጪ በሆኑ ማናቸውም ከ1 ኪሎ ግራም / 2.2 ፓውንድ/ በላይ በሚያጓጉዝ ኮንቴይነር ላይ መግለጫ መለጠፍ፣

ለ. በሚያንጉዝበት፣ በሚጭንበትና በሚያራግፍበት ጊዜ ንጥረ ነገሩ በመበተን፣ በመፈንዳት ቃጠሎ ወይም እሣት ለማስነሣት ምክንያት የሚሆን ነገር ያለመኖሩን ማረጋገጥ፣

ሐ. ተሽከርካሪው የእሣት ማጥፊያ እንዲኖረው ማድረግ፣

መ. በአካባቢው ወይም በሰው ጤና ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ፣

ሠ. ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም አደገኛ ዕቃ አለማጓጓዝ፣እና

ረ. አደገኛ ተብሎ የተመደበን ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ለማጓጓዝ ከአካባቢ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ፈቃድ ማግኘት፡፡

2. አሲድ ወይም ዝገት ነክ ንጥረ ነገር የተወሰነ ዓይነት ባትሪዎችን አይጨምርም፡፡ ዝርዝር መመሪያው በትራንስፖርት ሚኒስቴር መ/ቤት ይወጣል፡፡

## 6. ኦርጋኒክ ፐር ኦክሳይድ

የፔትሮሊየም ውሁደት ያለው ኦርጋኒክ ፐርኦክሣይድ አጓጓዥ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች መፈፀም አለበት፡-

1. እሣት ወይም ቃጠሎ እና ፍንዳታ የሚያስነሣ ፈሣሽ ወይም የራዲዮ ንጥረ ነገር፣ ከውሃ ጋር ሲገናኝ ተቀጣጣይ ጋዝ ሊያመነጭ የሚችል ወይም ነበልባል የሚያስነሣ እሣት ነክ ንጥረ ነገር በተሽከርካሪው አለመያዝ፣

2. በተሽከርካሪው ውስጥ የእሣት አደጋ ማጥፊያ መያዝ፣

3. አነስተኛ መጠን ያለው ውህድ ኬሚካል ወይም አሲድ /ዝገት ነክ ንጥረ ነገር/ አለመጫን፣

4. እሣት ወይም ፍንዳታ ለማስነሣት ምክንያት ሊሆን የሚችል ነገር ቀላቅሎ አለመጫን፣ እና

5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4/1 በተመለከተው መሠረት መግለጫ መለጠፍ፡ ፡

## 7. ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር ወይም ጋዝ

1. ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር ወይም ጋዝ የሚያጓጉዝ ባለ ተሽከርካሪ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 በተመለከተው መሠረት መግለጫ መለጠፍ የማያስፈልገው፤

ሀ. ከ 5 ሊትር / 1.1 ጋሎን/ የማይበልጥ ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር በያዘ ኮንቴይነር ላይ፣

ለ. አሴልዳይድ ወይም ካርቦን ዳይስልፋይድ በተጫነ ተሽከርካሪ ላይ ወይም ተቀጣጣይ ንጥረ ነገሩ ከ 1 ኪሎ በታች በሆነ ዕቃ ከተያዘ፣ እና

ሐ. ሌሎች ተቀጣጣይ ንጥረ ነገሮችን ሣይጨምር ከ5 ሊትር ያልበለጠ ለቤት ውስጥ የማገዶ ፍጆታ የሚውል ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር በጫነ ተሽከርካሪ ላይ ነው::

2. ማናቸውም አጓጓዥ ተንቀሣቃሽ መብራት፣ የሚፈነዱ ወይም ሌሎች በድንገት የእሣት ቃጠሎ ሊያስነሱ የሚችሉ ነገሮችን ተቀጣጣይ ፈሣሽ በጫኑ ተሽከርካሪ ላይ መጫን የለበትም::

3. ተቀጣጣይ ንጥረ ነገር ወይም ጋዝ የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ የእሣት ማጥፊያ መያዝ አለበት::

4. ከብረት የተሠራና ከ 50 ጋሎን ያላነሰ የመጫን አቅም ባላው ኮንቴይነር ወይም ቦቴ ካልሆነ በስተቀር ፔትሮሊየምን በማጓጓዝ ሥራ ላይ መሠማራት አይቻልም:: ሆኖም የሚጓጓዘው ንጥረ ነገር ውሁድ ከ 75% ያልበለጠ የፔትሮሊየም ድብልቅ የያዘ ከሆነ ኮንቴይነሩ ከ 340.65 ሊትር /90 ጋሎን/ የመጫን አቅም ያለው ሊሆን ይችላል::

5. ከ5677.5 ሊትር /1500 ጋሎን/ በላይ ፔትሮሊየም የመጫን አቅም ያለው ተሽከርካሪ ማንኛውንም ዓይነት ተሣቢ ሊጐትት አይችልም::

6. ፔትሮሊየም ለመጫን ብቻ የሚያገለግል ተሣቢ ፔትሮሊየምን በሚያጓጓዝ ተሽከርካሪ የሚሣብ ካልሆነ በስተቀር ተሣቢ አይኖረውም::

## 8. መርዛማ ቆሻሻ

መርዛማ ቆሻሻ የሚጓጓዝበትን ሁኔታ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል::

## 9. መርዝ

1. መርዝ በሚጓጓዝበት ጊዜ አደጋ እንዳያስከትል በበቂ ሁኔታ በወፍራም ነገር መታሸግ አለበት፤

2. የመርዙን ዓይነት የሚገልፅ መግለጫ በተጫነው ተሽከርካሪ ላይ መለጠፍ አለበት፤

3. አጓጓዡ የጫነው መርዝ ከምግብ ንክኪ ነፃ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት::

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Transport Authority No. 1

10. <u>ሬዲዮ አክቲቭ</u>

1. በግራም ከ 0.002 ማይክሮ ኩራይ የሚበልጥ ስበት ያለውን ማንኛውንም የሬዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገር በህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ወይም በማንኛ ውም አሲድ ወይም ዝገት ነክ ንጥረ ነገር በሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ መጓጓዝ የለበትም፣

2. የሬዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገር የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ ስለሚያጓጉዘው ሬዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገር የሚያመለክት መግለጫ መለጠፍ ይኖርበታል፣

3. የሚጓጓዘው የሬዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገር የሚፈነጥቀው መጠን በሰዓት ከ 2 ሚሊረም መብለጥ የለበትም፣

4. አጓጓዡ የሬዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገሩን ከማጓጓዙ አንድ ወር ቀደም ብሎ ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘትና በፍንጣቂው ሊኖር ስለሚችለው ተጋላጭነት መግለጫ መስጠት አለበት፣

5. ጨረር አመንጪ ቁስን ለማጓጓዝ ከጨረር መከላከያ ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት።

11. <u>የታመቀ ጋዝ</u>

የታመቀ ጋዝ የሚጓጓዝበት ሁኔታ የሚመለከተው አካል በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. <u>ቅጣት</u>

ይህንን መመሪያ የተላለፈ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥፋተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ በወንጀል ህግ መሠረት ይቀጣል።

13. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከግንቦት 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት 2006 ዓ.ም.

ካሳሁን ኃ/ማርያም
የትራንስፖርት ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1